የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No.1
ADDIS ABABA, 19th November, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ፲፬

በሀገር ህልውና እና ሉዓላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ገጽ…………………………………….፲፫ሺ፯፻፴፯

## Content

Proclamation No. 5/2021

A State of Emergency Proclamation Enacted to Avert the Threat Against National Existence and Sovereignty …...........................Page 13737

**አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ፲፬**

**<u>በሀገር ህልውና እና ሉዓላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ</u>**

መንግሥት የሀገርን ህልውና፣ ሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት ከውስጥም ሆነ ከውጭ ጠላቶች የመጠበቅ የሕግም ሆነ የሞራል ኃላፊነት እና ግዴታ ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፤

የሽብርተኛው ሕወሃት እና የሽብር ግብረአበሮቹ እንቅስቃሴ በሀገር ህልውና እና ሉዓላዊነት ላይ ጉልህ እና ድርስ አደጋ የደቀነ በመሆኑ፤

ሽብርተኛው ሕወሃት እና የሽብር ግብረአበሮቹ ለእኩይ ዓላማቸው መሳካት በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በንፁሃን ዜጎች ላይ እየፈጸሙ ያሉት ግድያ፣ ዝርፊያ እና ሌሎችም ከፍተኛ ጭካኔ የተሞላባቸው ኢሰብዓዊ ጥቃቶች እጅግ አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ከግምት በማስገባት፤

**PROCLAMATION NO. 5/2021**

**<u>A STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION ENACTED TO AVERT THE THREAT AGAINST NATIONAL EXISTENCE AND SOVEREIGNTY</u>**

**WHEREAS,** it is the government's legal duty and moral responsibility to safeguard the existence and sovereignty of the nation from internal and external enemies;

**WHEREAS,** the terrorist TPLF and its affiliates pose a grave and imminent danger against the existence and sovereignty of the country;

**CONSIDERING** the gravity of the killings, looting and other cruel and inhuman attacks that are being perpetrated by the terrorist TPLF and its affiliates against civilians in several parts of the country;

ከቀጥተኛ እና መደበኛ የውጊያ አውድ በተጨማሪም የሽብርተኛው ሕወሃት እና የሽብር ግብረአበሮቹን ተልዕኮ ያነገቡ ግለሰቦች ከሰላማዊ ዜጎች ጋር በመመሳሰል በሕዝብ እና በሀገር ላይ የደቀኑትን ከፍተኛ እና ተጨባጭ የደህንነት ስጋት በመረዳት፤

ሽብርተኛው ሕወሃት ኢትዮጵያን የማዳከም እና ብሎም የማፍረስ ምኞት ካላቸው የውጭ ኃይሎች ጋር በከፍተኛ ቅንጅት እየሰራ እንደሆነ በመገንዘብ፤

ከላይ የተገለጹት የሀገር ህልውና ላይ የተደቀኑ አደጋዎችን በመደበኛው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመቋቋም አዳጋች በመሆኑ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መደንገግ እና ተግባራዊ ማድረግ አደጋውን ለመቀልበስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፺፫(፩) ፊደል-ተራ (ሀ) መሰረት የሚከተለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በሀገር ህልውና እና ሉዓላዊነት ላይ የተደቀነን አደጋ ለመከላከል የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል፦

፩/ **"የሕግ አስከባሪ አካል"** ማለት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልል ፖሊስ እና ሌሎች የፀጥታ አካላት ማለት ነው፤

**COGNIZANT** of the severity of the threat posed by individuals who live among the civilian population and work as operatives of the TPLF and its terrorist affiliates to the security of the state and the nation;

**COGNIZANT** of the fact that the terrorist TPLF is working in close cooperation with foreign powers that desire to weaken and destroy Ethiopia;

**WHEREAS,** it has become necessary to declare and implement a state of emergency in order to avert the above mentioned imminent threats against the existence of the nation which cannot be averted by regular law enforcement mechanisms;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 93(1) paragraph (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**PART ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "State of Emergency Proclamation Enacted to Avert the Threat Against National Existence and Sovereignty No. 5/2021".

2. **Definition**

For the purposes of this Proclamation:-

1/ **"Law Enforcement Organ"** means Ministry of Defence, National Intelligence and Security Service, Federal Police Commission, Regional States Police, and other security organs;

፪/ **“የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ”** ማለት የዚህን አዋጅ አፈጻጸም ለመከታተል እና በበላይነት ለመምራት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት የተቋቋመ የአስቸኳይ ጊዜ መምሪያ ዕዝ ነው፤

፫/ **“የጦር መሳሪያ”** ማለት በጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፸፯/፪ሺ፲፪ ትርጉም የተሰጣቸውን አነስተኛ፣ ቀላል እና ሌሎችንም የጦር መሳሪያ ዓይነቶች እና ጉዳት አድራሽ ዕቃዎች ያጠቃልላል፤

፬/ **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

፭/ በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል።

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

፩/ ይህ አዋጅ በመላው ኢትዮጵያ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአደጋው መጠን እና አካባቢያዊ አድማስ እየቀነሰ በሄደ ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን በዚያው ልክ እየጠበበ ሊሄድ የሚችል ሲሆን፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ የአዋጁ ተፈጻሚነት በከፊልም ሆነ በሙሉ ቀሪ የሚሆንባቸውን አካባቢዎች በመመሪያ ይወስናል፣ ይህንኑ ለሕዝብ ያሳውቃል።

2/ **“State of Emergency Operation Command”** means the command established under Article 7 of this Proclamation to follow up and to lead its implementation;

3/ **“Firearms”** means weapons that are defined under Firearm Administration and Control Proclamation No. 1177/2020 that includes small firearms, light firearms, and other weapons and harm inflicting materials;

4/ **“Person”** means any physical or juridical person;

5/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Scope of Application</u>**

1/ This Proclamation shall be applicable in all parts of Ethiopia.

2/ Without prejudice to the Provision of Sub-Article (1) of this Article, the scope of application of this Proclamation could be narrowed contingent on the magnitude of the problem that necessitated this Proclamation. The State of Emergency Operation Command shall determine, through Directives, parts of the country where the application of this Proclamation would be lifted and publicize the same to the public.

## ክፍል ሁለት

## በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎችና የማይፈቀዱ ተግባራት

**፬. በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች**

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ የሀገርን ህልውና እና ሉዓላዊነት፣ እንዲሁም የሰላማዊ ዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን፡-

፩/ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል መከላከያ ኃይልን ወይም የትኛውንም ሌላ የፀጥታ አካል በማሰማራት ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤

፪/ እድሜያቸው ለወታደራዊ አገልግሎት የደረሱ እና የጦር መሳሪያ የታጠቁ ዜጎች ወታደራዊ ስልጠና እንዲወስዱ፣ ወታደራዊ ግዳጅ እንዲቀበሉ፣ ወይም ይህን ማድረግ የማይችሉ ሲሆን በአማራጭ ትጥቃቸውን ለመንግስት እንዲያስረክቡ ሊያዝ ይችላል፤

፫/ የሰዓት ዕላፊ ገደብ ሊወሰን ይችላል፤

፬/ ማናቸውም የሕዝብ የመገናኛ እና የሕዝብ መጓጓዥ ዘዴ እንዲዘጋ ወይም እንዲቋረጥ ሊያዝ ይችላል፤

፭/ ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራል ብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ሥር ለማድረግ፣ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ሆኖ ባለበት ጊዜ ድረስ ይዞ ለማቆየት ወይም በመደበኛ ሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ይችላል፤

## PART TWO

## EMERGENCY MEASURES AND PROHIBITED ACTIONS

**4. State of Emergency Measures**

When the State of Emergency Operation Command believes that it is necessary to protect the existence and sovereignty of the nation and to maintain the security of innocent civilians, it may:-

1/ Order the deployment of the armed forces or other security forces in any part of the country to maintain peace and security;

2/ Order citizens whose age are fit for military service and who are in possession of firearms to take military training, to take orders for military missions, or to hand over their firearms in case they are unable to do so;

3/ To Impose curfew;

4/ Cause the closure or termination of any means of communication and public transportation;

5/ Arrest any person without a court warrant upon reasonable suspicion that he cooperates with terrorist groups; detain such person for the period that this Proclamation is in force or hold the same accountable under the law;

፮/ ከሽብር ቡድኖች ጋር ይተባበራል ብሎ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ወይም ድርጅት ንብረት የሆነን ማንኛውንም ቤት፣ ህንፃ፣ ቦታ፣ መጓጓዣ ለመበርበርና እንዲሁም ማንኛውንም ሰው ለማስቆም፣ ማንነቱን ለመጠየቅ፣ ለመፈተሽ ይችላል፤ በብርበራ ወይም በፍተሻ የተያዙ የጦር መሳሪያዎችን መውረስ ይችላል ፤

፯/ ለተወሰነ ጊዜ መንገዶችን፣ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ለመዝጋት እንዲሁም ሰዎች ለጊዜው በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ፣ ወደተወሰነ አካባቢ እንዳይገቡ ወይም ከተወሰነ ቦታ እንዲለቁ ለማዘዝ ይችላል፣

፰/ ከፍተኛ የፀጥታ ችግር እና ስጋት በተፈጠረባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች የአካባቢ አመራር መዋቅርን በከፊልም ሆነ በሙሉ፣ ማገድ፣ መለወጥ እና በሲቪልም ሆነ በወታደራዊ አመራር መተካት ይችላል፤

፱/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የሞራልም ሆነ የቁስ ድጋፍ ያደርጋል ብሎ የሚጠረጥረውን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት እንቅስቃሴ በሚመለከተው ባለስልጣን በኩል እንዲታገድ ወይም ፈቃዱ እንዲሰረዝ ሊያዝ ይችላል፤

፲/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የሞራል ድጋፍ ያደርጋል ብሎ የሚያምነውን የመገናኛ ብዙሃን ወይም ጋዜጠኛ በሚመለከተው ባለስልጣን በኩል እንዲታገድ ወይም ፈቃዱ እንዲሰረዝ ሊያዝ ይችላል፡፡

6/ Search any person's house, building, place, and vehicle upon reasonable suspicion that he cooperates with terrorist groups; stop any person to search and to ascertain his identity; confiscate seized firearms;

7/ Give order for the closure of a given street or a service providing institution for a certain period; or give an order for persons to stay in a certain place, ban from entering into or evacuate from a given place for a certain period;

8/ Partially or fully suspend local administrative structure, change or replace administrators with civilian or military administrators in parts of the country where there are serious security threats and problems of the country;

9/ Order the relevant regulatory authority to effect the suspension or permanent cancellation of licenses of civil society organizations which have been suspected of providing direct or indirect, moral or material support to terrorist organizations;

10/ Order the relevant regulatory authority to effect the suspension or permanent cancellation of licenses of mass media or journalists who have been suspected of providing direct or indirect, moral or material support to terrorist organizations.

**፭. ተመጣጣኝ ኃይል ስለመጠቀም እና የማይታገዱ መብቶች**

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሕግ አስከባሪ አካላት ተመጣጣኝ ኃይል እንዲጠቀሙ መመሪያ ለመስጠት ይችላል።

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በሚያወጣቸው መመሪያዎች፣ በሚወስናቸው ውሳኔዎች እና በሚወስዳቸው እርምጃዎች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፺፫ ንዑስ-አንቀጽ (፬) ፊደል-ተራ (ሐ) መሰረት ሊታገዱ የማይችሉ የሕገ መንግስት ድንጋጌዎችን እና መብቶችን ማክበር ይኖርበታል።

**፮. የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎች**

፩/ ሁሉም ሰው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በአዋጁ መሰረት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች እና የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች የመቀበል ግዴታ አለበት።

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙን እንቅስቃሴ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ዓላማ የሚቃረን፣ የሚቃወም እና ለሽብር ቡድኖች ዓላማ መሳካት አስተዋፅኦ የሚያደርግ፣ የሽብር ቡድኖችን የሚያበረታታ፣ ሰላማዊ ዜጎችን የሚያሸብር ንግግር በማንኛውም መንገድ ማድረግ ወይም ማሰራጨት የተከለከለ ነው።

፫/ በየትኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሽብር ቡድኖች የገንዘብ፣ የመረጃ፣ የቁስም ሆነ የሞራል ድጋፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

**5. Use of Proportional Force and Non Derogable Rights**

1/ The State of Emergency Operation Command may order security forces to use proportional force which it finds necessary for the execution of state of emergency measures provided in this Proclamation.

2/ The State of Emergency operation command shall respect the provisions and rights enshrined under Article 93 Sub-Article (4) Paragraph (c) of the FDRE Constitution on its Directives, decisions, and measures.

**6. Obligations and Prohibited Activities**

1/ Any person shall have the duty to observe Directives and Orders of the Emergency Operation Command enacted in accordance with this Proclamation.

2/ Any form of expression which is opposed to the operation of the Emergency Operation Command and the purpose of the Proclamation, contributes to the success of terrorist groups' objectives, encourages the activities of the terrorist group, or terrorizes civilian population is prohibited.

3/ Providing any form of monetary, information, material, or moral support, either directly or indirectly, to terrorist groups is prohibited.

፬/ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በተዋረድ ውክልና ከሰጣቸው አካላት ፈቃድ ውጪ ማንኛውንም የአደባባይ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

፭/ ከመከላከያ፣ ከፌደራል ፖሊስ ወይም ሌሎች ፈቃድ ከሚሰጣቸው የፀጥታ አካላት ወይም ከእነዚህ አካላት እውቅና እና ፈቃድ ውጭ ማናቸውንም የጦር መሳሪያ ይዞ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

፮/ በከተሞች አካባቢ የነዋሪ መታወቂያ ፣ የመንጃ ፈቃድ፣ የሰራተኛ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም ከነዚህ ተመጣጣኝ የሆነ መታወቂያ ሳይዙ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው። ከነዚህ የመታወቂያ ሰነዶች መካከል የትኛውም የሌለው ሰው ይህን ጉዳይ በተመለከተ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ባወጣ በሁለት ሳምንት ውስጥ በአቅራቢያው በሚገኝ የቀበሌ፣ የወረዳ የፀጥታ እና አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ወይም ፖሊስ ጣቢያ በመመዝገብ ጊዜያዊ የመታወቂያ ወረቀት የመያዝ ግዴታ አለበት።

፯/ ማንኛውንም ወሳኝ በሆነ የአገልግሎት ዘርፍም ሆነ በምርት ሂደት ላይ የሥራ ማስተጓጎል ወይም የኢኮኖሚ አሻጥር መፈጸም የተከለከለ ነው።

፰/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አፈጻጸም ሰበብ በማድረግ የግል ጥቅም ለማግኘት ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ሳይኖር ሆን ብሎ ዜጎችን ማሰር ወይም መሰል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው።

4/ Holding demonstrations or public gathering without permission of the Emergency Operation Command or any other delegated authority is prohibited.

5/ Moving around with firearms without the permission from National Defense Force, Federal Police, or other relevant security institutions is prohibited.

6/ Moving around cities without holding an identity card, driving license, employee identity card, passport, or any other similar identity card is prohibited. Any person who does not have an identity card shall acquire a temporary identity card from nearby local Kebele, Woreda Security and administration office, or police station within two weeks from the issuance of a Directive regarding this matter by the Emergency Operation Command.

7/ Disrupting the activities of any essential service or production sector or carrying out acts of economic sabotage is prohibited.

8/ Engaging in abuse of power with intent to gain an illicit benefit under the pretext of enforcing the Proclamation or detaining individuals deliberately without reasonable suspicion or engaging in any such abusive behavior is prohibited.

## ክፍል ሶስት

## ስለ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ

**፯. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ መቋቋምና ኃላፊነት**

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚያስፈጽም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማገር ሹም የሚመራ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ" ተቋቁሟል።

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ መዋቅር እና አደረጃጀት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወሰን ይሆናል።

፫/ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ አግባብነት ካላቸው አካላት የተውጣጡ እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ኃላፊነት ወስደው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተፈጻሚ የሚያደርጉ ግብረሃይሎችን ወይም ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል።

፬/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ ተጠሪነት ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል።

፭/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተመለከቱ እርምጃዎችን ተፈጻሚነት ይመራል፣ ይከታተላል።

፮/ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በሀገሪቱ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላትን በአንድ ዕዝ ሥር አድርጎ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያዛል።

፯/ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉ ሌሎች አስፈላጊ እና አግባብ የሆኑ ሥልጣኖች ይኖሩታል።

## PART THREE

## STATE OF EMERGENCY OPERATION COMMAND

**7. Establishment and Responsibility of State of Emergency Operation Command**

1/ A body led by the Chief of Staff of the Ethiopian National Defense Forces hereinafter referred to as "State of Emergency Operation Command'' is hereby established to enforce this Proclamation.

2/ The structure and organization of the State of Emergency Operation Command shall be determined by the Prime Minister.

3/ The State of Emergency Operation Command may establish task forces and committees from relevant bodies which will take responsibilities for the enforcement of this Proclamation.

4/ The State of Emergency Operation Command is responsible to the F.D.R.E Prime Minister.

5/ The State of Emergency Operation Command shall lead and monitor measures stated under Article 4 of this Proclamation.

6/ The State of Emergency Operation Command shall lead, coordinate and order law enforcement organs under one command.

7/ It shall have any other power necessary and proper for the execution of its powers under this Proclamation.

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፰. ተፈጻሚነታቸው የታገዱ ሕጎች

፩/ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እስኪጠናቀቅ ድረስ የትኛውም የዳኝነት አካል ሥልጣን አይኖረውም።

፪/ በቪዬና ኮንቬንሽን እና በአስተናጋጅ ሀገር ስምምነቶች የተመለከቱት የዲፕሎማቲክ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የፍሬ ነገርና የሥነ-ሥርዓት ሕጎች ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ተፈጻሚነታቸው ታግዶ ይቆያል::

### ፱. የወንጀል ተጠያቂነት

፩/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እንደጥፋቱ ክብደት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ የተፈጸመው ወንጀል በሌሎች ሕጎች ከዚህ ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ የከበደው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆናል።

፫/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት የተፈጸሙ የአዋጁ እና በአዋጁ ማዕቀፍ የወጡ መመሪያዎች ጥሰቶች የአዋጁ ተፈጻሚነት ጊዜ ቢያበቃም፣ የሚያስከትሉት የወንጀል ተጠያቂነት በመደበኛው የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሰረት ይቀጥላል።

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 8. Suspended Laws

1/ Any judicial organ shall not have authority with regards to the enforcement of this Proclamation until the expiry of the same.

2/ Without prejudice to diplomatic immunities indicated under the Vienna Convention on Diplomatic Relations and Host Country Agreements, substantive and procedural laws inconsistent with this Proclamation shall remain suspended during the implementation of this Proclamation.

### 9. Criminal Liability

1/ Whosoever violates the provisions of this Proclamation or Directives issued in accordance with this Proclamation shall be punished with simple imprisonment of up to three years or depending on the gravity of the offense rigorous imprisonment of up to ten years.

2/ Crimes committed in violation of the provisions of this Proclamation or Directive issued in accordance with this Proclamation entails grave punishment in other Laws, such punishment shall apply.

3/ Violations of this Proclamation and Directives issued pursuant to it that have been committed during the course of this State of Emergency will entail criminal liability in accordance with ordinary criminal procedure rules even after the expiry of the state of emergency.

**፲. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዙ በአዋጁ የተሰጠውን ሥልጣን ተግባራዊ ለማድረግ እና ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ መመሪያዎችን ያወጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወጡ መመሪያዎች ተፈጻሚ ከመደረጋቸው በፊት ለሕዝብ በስፋት ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ እንዲተዋወቁ መደረግ ይኖርበታል።

**፲፩. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

፩/ ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታወጀበት ከጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ ለስድስት ወራት የጸና ይሆናል።

፪/ የስድስት ወር ጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአዋጁ ተፈጻሚነት ቀሪ የሚሆንበትን ጊዜ ሊወስን ይችላል።

**አዲስ አበባ ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**10. <u>Power to Issue Directive</u>**

1/ The State of Emergency Operation Command may issue Directives for the implementation of this Proclamation

2/ Directives issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be notified to the public through mass media that is widely accessible to the general public before their implementation.

**11. <u>Effective Date</u>**

1/ This State of Emergency Proclamation shall remain in effect for six months starting from 2nd day of November, 2021 since the time promulgated by the Council of Ministers.

2/ The House of Peoples Representatives may determine the cessation time of the Proclamation before the end of the six months period.

**Done at Addis Ababa, On this 19th day of November, 2021**

**ABIY AHMED (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**